# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

# OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳኛ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፴ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 61
ADDIS ABABA , 6 th ,August ,2025


## ማውጫ


**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፪/፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

ለፍጥነት መንገድ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከአለም ዐቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ……………………………………….ገፅ ፲፱ሺ፺፪


## CONTENT


**PROCLAMATION NO. 1392/2025**

International Development Association Loan Agreement for Additional Financing for Express way Development Support Project Ratification Proclamation………...Page 19092


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፪/፪ሺ፲፯ ዓ.ም

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለፍጥነት መንገድ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ሀያ ሰባት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ. አር (፳፯ ሚሊዮን ፫፻ሺ ኤስ.ዲ .አር) ተጨማሪ ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

## PROCLAMATION NO.1392/2025

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMNT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHERE AS,** the Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association to stipulating that the International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to twenty seven million three hundred thousand Special Drawing Rights (SDR

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ባካሄደው ፪ኛ ልዩ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩.<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለፍጥነት መንገድ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከአለም ዐቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፺፪/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪.<u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር-7900 ET በዚህ አዋጅ ፀደቋል፡፡

፫. <u>የገንንዘብ ሚኒስቴር ስልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሀያ ሰባት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ. አር(፳፯ሚሊዮን፫፻ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ

27, 300, 0000) for Additional Financing for Expressway Development Support Project, was signed in Addis Ababa on 25th day of June, 2025,

**WHERE AS**,this loan agreement was approved by the House of Peoples' Representatives of the F.D.R.E during its 2nd extraordinary session held on 4th day of July ,2025;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub articles (1) and (12) of the F.D.R.E Constitution, it is hereby Proclaimed as follows:

1.**<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the 'International Development Association Loan Agreement for Additional Financing for Express way Development Support Project Ratification Proclamation No.1392 /2025.

2. **<u>RATIFICATION OF THE AGREEMENT</u>**

The Loan Agreement Number 7900- ET signed in Addis Ababa on 25th day of June 2025 between the Federal Democratic Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified by this Proclamation.

3.**<u>POWER OF THE MIISTRY OF FINANCE</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to twenty seven million three hundred thousand Special Drawing Rights( 27,300,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement by

አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፴ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

this Proclamation.

4.**Effective Date**

This Proclamation shall enter in to force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, this 6th of August 2025**

**TAYE ATSEKESELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**

.